# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT** | جبهة تحرير اورومو

Gaafa: 14/12/2015
Date: تاريخ

Lakk.: 17/stm - abo/2015
No.: رقم

**የትግል ጥሪ**

**ለመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች!**

**የመንግስት በደል ለሚሰማቸው ለመላው የተጨቋኝ ህዝቦች ተወላጆች!**

***መላውን ጎረቤት እያዳረሰ ያለውን ይህንን እሳት በጋራ እናጥፋ!***

የኦሮሞ ተማሪዎችና ወጣቶች ከህዳር 12 ቀን 2015ዓም ኣንስቶ ባቀጣጠሉት ኣዲስ ንቅናቄ የህይወትና ለኣካል ጉዳት በመዳረግ ከባድ መስዋዕትነት እየከፈሉ ይገኛሉ።

ህዝባችን ይህንን መስዋዕትነት እየከፈለ ያለው በተፈጥሮ ያለውን መብቱንና የመሬት ባለቤትነቱን ለማረጋገጥና መብቱን ለማስከበር ሲል ነው። ይህን መሰሉ ፍልሚያ ደረጃው ይበላለጥ እንጂ በመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ጓዳ እየተካሄደ ይገኛል። ከጎንደር መሬት ተቆርሶ ለባዕድ እየተሰጠ ነው። የመሬቱ ባለቤት የሆነው የጋምቤላ ህዝብ ከመሬቱ ተፈናቅሎ ከውጪ ለመጡ ባዕዳን እየተሸጠ ነው። ከኦሞ ውስጥም ህዝቦች እየተፈናቀሉ ይገኛሉ። ሌሎችንም በርከት ያሉ መሰል ዝርዝሮችን ማቅረብ ይቻላል። ይህ ሁሉ የኦሮሞ ህዝብ ፊንፊኔን ኣስመልክቶ እያነሳ ካለው ጥያቄ ጋር ተማሳሳይነት ኣለው።

የኦሮሞ ህዝብ በሰላማዊ መንገድ በመታገል ላይ ባለበት በኣሁኑ ወቅት ጉዳዩ እኔ ላይ ኣልደረሰም ብሎ ዳር ቆሞ መመልከት ኣይቻልም። ዛሬ በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ነገ ወደናንተም መድረሱ ስለማይቀር በዝምታ መመልከታችሁ ቁጭትን ይፈጥራል።

ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የወያኔ መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ህዝቦች ላይ እያደረሰ ያለውን ጭቆና በዝምታ የምንመለከትበት ወቅት ኣይደለም። ኢትዮጵያን ሲያስተዳድሩ የነበሩትና እያስተዳደሩ ያሉት ስርዓቶች በህዝቦች መካከል መጠራጠርንና ፍራቻን ፈጥረዋል። ኣሁን ከኢትዮጵያ ህዝቦች የሚፈለገው ካያሉበት ተነስተው የወያኔ ኢህኣዴግ መንግስትን ከላያቸው ላይ ማሽቀንጠር ነው።

**ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝቦች ሆይ!**

**መብታችሁንና ጥቅማችሁን ለማስከበር ከሁሉም ቦታ ተንቀሳቀሱ!**

**የኦሮሞ ህዝብ እያደረገ ካለው እንቅስቃሴ ጎን ተሰለፉ!**

በወያኔ ሰራዊት፣ ፖሊስና የደህንነት ሃይል ውስጥ ያላችሁ ዜጎች ኦሮሞን ከመግደል ተቆጠቡ! የወያኔ መንግስት ኣብቅቶለታል።

እጅ ለእጅ ተያይዘን ይህንን መንግስት በመጣል ህዝቦች የሚሹትን ነጻነት፣ ዲሞክራሲ፣ ሰላምና መረጋጋት ለማገኘት እንንቀሳቀስ! የጎረቤትህ ቤት እየተቃጠለ የኔ በሰላም ይወጣል ብለህ ኣትጠብቅ። በጎረቤትህ ላይ የተቀጣጠለው እሳት ያንተንም ማቃጠሉ ኣይቀርምና!

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**እጅ ለእጅ ተያይዘን የወያኔን መንግስት እናስወግድ!**

P.O. Box 6973 Asmara, Eritrea Tel 2911 110236 Email: Caalchis@gmail.com, *www.oromoliberationfront.org*